አፍሪካ ቲቪ

5

# አፍሪካ አካዳሚ

## AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም

6

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ሙስሊም የሆነች ሴት ልትከለከል የሚገባት (ሐራም ከሚሆንባት) ነገር መካከል፡-

ለውበት ምክንያት ብሎ ጥርስን ቦርብሮ ለማሳመር መሞከር ነው፡፡

- ጥርስ የሚስተካከለው ለህክምና ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ሲፈጠር፣ ተቦርቡሮ፣ አደጋ ደርሶበት እና የግድ መስተካከል አለበት ተብሎ ብቻ መሆን አለበት እንጂ የአሏህን ፍጥረት መቀየር ስለሚሆን ለቁንጅና ብቻ ብሎ ጥርስን ማስተካከል በኢስላም የተከለከለ ነው፡፡
- ሌላው እንዴት አማኝ የሆነች ሴት ልትከከል ከሚገባት ነገሮች መካከል፡-
- ንቅሳት ወይም ውቅራት የሚባለው ነገር ሐራም ነው፡፡

ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ፡- “አሏህ እጅን ወይም እግርን፣ ፊት ላይ የሆነ ነገር የምትነቀስ እና የምታስነቅስን ረግመዋል” ብለዋል

- ይህ ከተላላቅ ወንጀሎች ስለሚመደብ ከተቻለ ለማስወገድ መሞከር እና ተውባ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ፀጉርን በሌላ ቀለም ማቅለምን በተመለከተም ጥቁር ቀለም ባልሆነ ነገር ግን በሌላ ቀለም መቀየር ይፈቀዳል፤ እጮኛን በማያታልል መልኩ ፀጉሯን ከጥቁር ቀለም በስተቀር በፈለገቸው ከለር ማቅለም ትችላለት፡፡ ጥቁር ግን የተከለከለ ነው፡፡
- የሌላ ሴት ፀጉርም ሆነ የእንስሳ ፀጉር በፀጉሯ ላይ መቀጠል ክልክል ሐራም ነው፡፡ ከአካላቷ መካከል አንዱንም መነቀስ ክልክል ነው፡፡ ሁለቱም ተግባሮች ከታላላቅ ወንጀሎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ነብዩ ቡኻሪና ሙስም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ቀጣዩም አስቀጣዩም ነቀሷም ተነቃሷም የአላህ እርግማን ይውረድባቸው›› ብለዋል፡፡
- ሴቶች ሒና ለእጅ እና እግር መቀባት በተለይ ስታገባ ወይም ለባሏ ቁንጅና መጠቀም በሱናም ይወደዳል፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

- ሴት ልጅ ለመዋብ ከሚፈቀዱላት ነገሮች መካከል ወርቅ ወይም ብርን እንዲሁም ወርቅ እና ብር ቅብ የሆኑ ለጌጣ ጌጥነት መጠቀም ነው፡፡
- ይህም በተለይ በቤት ውስጥ ለባሏ እና ለቅርብ ዘመዶቿ እንጂ ለሌሎች ይህን ጉዳይ መደበቅ እና ተሰትራ መሆን አለባት፡፡

5

አፍሪካ አካዳሚ

- ሴቶች ሊከለከሉ እና ሐራም ከሚሆንባቸው ነገሮች ወንዶች ወደነሱ እንዲመለከቱ መጋበዝ እና ለመታየት በሚል አስፈላጊ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ነው፡፡ ይህም ወንዶች ላይ ፊትና ስለሚሆን እና ስለሚረብሽ ሐራም ይሆንባታል፡፡
- በመንገዱ ላይ ወንዶች እንደሚኖሩ ያወቀች ሴት ሽቶ ተቀብታ በእነሱ አጠገብ ማለፍ የለባትም፡፡ ነቢዩ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ሴት ሽቶ ተቀብታ ወንዶች ሽታውን እንዲያጣጥሙላት ብላ ከወንዶች አጠገብ ካለፈች እሷ እንደዚህ (ዝሙተኛ) ናት›› ብለዋል፡፡
- አንዲት አማኝ ሴት ልትከለከል እና ሐራም ከሚሆንባት ነገሮች መካከል ለወንዶች የጌጥዋን ድምጽ ማሰማት ነው፡፡